በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት
ኮሚሽን

**Addis Ababa City Administration**
**Farmers and Urban Agriculture**
**Development Commission**

ቀን 21/3/15
Date

ቁጥር 3084/17/15
No.

ለቦሌ ክ/ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት
ለየካ ክ/ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት
ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት
ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት
ለኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት
ለለሚ ኩራ ክ/ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት
አ/አ/ከ/ግ/ል/ኮ

ጉዳዩ፡- የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ አፈፃፀም መመሪያ ስለመላክ!

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ 74/2014 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በአስተዳደር ስነ-ስርአት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት አድርጎ ያዘጋጀውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ በቁጥር 38/02-03/0723 በቀን 02/02/2015ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል፡፡

በዚሁ መሰረት የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ ተግባራዊነት ላይ መመሪያውን አውቃችሁት አርሶ አደሩ መመሪያውን አውቆ በዘርፉ ማግኘት ያለበትን ፍትሃዊ ጥቅም እንዲያገኝ ግንዛቤ እንዲትፈጥሩ ይረዳ ዘንድ ከመስሪያ ቤቱ የተላከውን መመሪያ 22 ገጽ ኮፒ አባሪ አድርገን ከዚህ ደብዳቤ ጋር የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ!

- ለዋና ኮሚሽነር
- ለም/ኮ/አርሶ አደር ማቋቋምና ሬትላቶሬ ዘርፍ
- ለአ/አ/ማቋቋምና ልማት ዳይሬክቶሬት
  አ/አ/ከ/ግ/ል/ኮ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
Addis Ababa City GOVERNMENT Environmental Protection Authority

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተግባራት

የአካባቢ ብክለት ...ግትና ህግ ተከባሪነትና አካባቢና ማህበረሰብ ...ጽእኖ ግምገማን ...ተግበር

የአየር ንብረት ...ውጥና ክትትልና ...ናት ማከናወን

የአማራጭ ኢነርጂ ...ከና ... ማስተዋወቅና ...ግግር ማድረግ

የማእድን ፍቃድ ...ሰጠት አስተዳደርና ...ቆጣጠር

የነዳጅና የነዳጅ ...ጤቶች ተቋማት ...ቃት ማረጋገጫ ...ሰጠትና መቆጣጠር

የስርዓተ ምህዳርና ...ህይወት ተግባራት ...ተፋሰስ እና አረንጓዴ ...ካቢዎች ፈቃድና ...ቃት ...ረጋገጫ ...ሰጠት

የአካባቢ ትምህርትና ...ንዛቤ ስራዎችን ...ተግበር

...11-6-33-41-30
p.o.box 6713
... የጥቆማ ስ.ቁ. 5674
...legram@addisEPA
...@addisenvironment.gov.et
...w.addisenvironment.gov.et
...ድ ሾላ ክአትሌቲክስ ...ሬሽን 200ሜ. ...ባ ...

653
19/3/15

ቁጥር 38/02-03/0723
ቀን 02/02/2015

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን
**አዲስ አበባ**

**ጉዳዩ፡-የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ አፈጻጸም መመሪያ ስለመላክ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ 74/2014 በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት በአስተዳደር ስነስርአት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት አድርጎ ያዘጋጀውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ የላክንላችሁ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

**ግልባጭ**

- ለማዕድን ፍቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት(ያለ አባሪ)
- ለህግ አገልግሎት ቡድን (ያለ አባሪ)

እ/ተ/ባ

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

# የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም

# መመሪያ ቁጥር /2014

መግቢያ

የኮንስትራክሽን ሥራዎች እና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች በቀጥታ በግብአትነት እየዋለ የሚገኘውን በከተማዋ ክልል የሚገኙ ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በማጥናት የማዕድን ማምረት ፈቃድ መስጠትና ማስተዳደር በማስፈለጉ፣

ከዘርፉ የሚሰበሰብ ልዩ ልዩ የሚሆን ገቢ ከሮያሊቲና ከሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች መሰብሰብ እንዲሁም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ሥራ አጥነትን ለመቀነስ በሚደረገው ርብርብ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ማበርከት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ውስን የሆነውን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ በመጠቀም የከተማዋ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያንዳንዱ ባለድርሻ በፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር በማምረትና በገቢ አሰባሰቡ ፣በመረጃ አያያዝና አቀራረብ፣ያለውን ኃላፊነት ተጠያቂነት ሊያሳይ የሚችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር…… /2014 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ውል"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንና በባለፍቃዱ መካከል የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረትና የማምረቻ ማሽን መትከያ ፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ስምምነት ነው፡
2. **"ማዕድን"** ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር ወይም በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም በመሬት ውስጥ፣በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ማለት ነው፡
3. **"አዋጅ"** ማለት የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 ከነማሻሻያው ነው፡
4. **"ደንብ"** ማለት የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 423/2010 ነው፡
5. **"የፈቃድ ሰጪው መስሪያ ቤት"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡
6. **"የኮንስትራክሽን ማዕድን"** ማለት ማናቸውም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኮንስትራክሽን በግብዓትነት የሚያገለግል ጥቁር ድንጋይ ፣ አሸዋ ፣ ነጭ ድንጋይ ፣ የሸክላ አፈር ፣ እና ሌሎች ብረት ነክ ያልሆኑ ማዕድናትን የሚያጠቃልል ነው፡
7. **"ክምችት"** ማለት በከርሰ ምድር ውስጥ በአንድ በተወሰነ ስፍራ በተፈጥሮ የሚገኝ የኮንስትራክሽን ማዕድናትና ማዕድን ነው፡
8. **"ፈቃድ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የኮንስትራክሽን ማዕድናት ለማምረት፣የማምረቻ ማሽን ለመትከል በጊዜና በቦታ ተወስኖ የተሰጠ ፈቃድ ነው፡
9. **"የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ"** ማለት ከማእድኑ ሥፍራ በዓመት የሚመረተው የማእድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠኑ ከ80ሺ. ሜ.ኩ በላይ የሆነ የማዕድን ማምረት ሥራ ሲሆን የማዕድን ማምረቻ ቦታው ስፋት ከ30ሺ.ካ.ሜ በላይ እስከ 100ሺ.ካሬ.ሜ. ሆኖ የማዕድኑ ዓይነት ጥቁር ድንጋይ ነው፡
10. **"መካከለኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ"** ማለት ከማእድኑ ሥፍራ በዓመት

12. "**ፈቃድ ክልል**" ማለት ማናቸውም ለኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረቻ ማሽን መትከያ ፈቃድ የተሰጠበት ስፍራ ነው፡

13. "**ማምረት**" ማለት የኮንስትራክሽን ማዕድናት ከክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚከናወን ተግባር ሲሆን ማዕድናትን ማከማቸትን ማዘጋጀትን ወይም ማጓጓዝን የሚያካትት ሲሆን ማቅለጥን አይጨምርም፡

14. "**እምርቶ የመሸጥ ፈቃድ**"ማለት ማዕድኑን እምርቶ ለገበያ ማዋል ነው፡

15. "**እምርቶ የመጠቀም ፈቃድ**"ማለት ምርቱን እምርቶ ለራስ ወይም ለመንግስት ልማት ማዋል ነው፡

16. "**የምርት ማንሻ ፈቃድ**" ማለት ፈቃዱ በተለያየ ምክንያት ሲሰረዝ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ተመርቶ የተከማቸ ምርት ሲኖር እንደምርቱ መጠን በጊዜያዊነት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡

17. "**የማዕድን ስራዎች**" ማለት የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ለማምረት የሚካሄድ ማንኛውም ተግባር ነው፡

18. «**አልሚ**» ማለት የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት ወይም ማህበር ነው፡

19. "**ሮያሊቲ**" ማለት የማዕድን ሀብት ባለቤት ለሆነው መንግስትና ህዝብ ባለፈቃዱ ከማዕድን ማምረቻ ቦታ ላይ ከሚያመርተው የማዕድን ምርት በየጊዜው በመቶኛ እየተሰላ የማምረቻና ሪስክ ወጭን ሳይጨምር የሚከፈል ክፍያ ነው፡

20. "**የሥራ ፕሮግራም**" ማለት ማዕድን ለማምረት የሚቀርብ የስራ ዝርዝር ሲሆን፤ ሥራው የሚከናወንበት ጊዜ፤ ወጭውን መዋቅሩን የሚያመላክት እቅድ ነው፡

21. "**ማስተላለፍ**" ወይም ስም ማዛወር ማለት መሸጥ፣በእዳ ማስያዝ ማውረስ መዴረግ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው፡

22. "**የፈቃድ ስም ለውጥ**" ማለት ቀደም ሲል በተሰጠው የማዕድን ማምረት ፈቃድ መሰረት ምንም አይነት የባለቤትነት ለውጥ ሳይኖር ወይም ባለቤትነትን ሳያጣ የፍቃዱ ስም ለውጥ ብቻ ሲደረግ ነው፡

23. "**የማምረቻ ማሽን መትከያ**" ማለት ለማዕድን ማምረቻነት በቀጥታ የሚያገለግሉ የድንጋይ መፍጫ ማሽንን ለመትከል፤ ሎደር ዶዘር እና የመሳሰሉትን ማሽነሪዎችን ማስቀመጫና የምርት ማከማቻ ቦታ ሲሆን በተጨማሪም ምርቱን በግብዓትነት ለመጠቀም የሚያስችሉ ከማምረቻው አካባቢ ርቀው ቢከናወኑ ኢኮኖሚያዊ እና

ስነምህዳራዊ አዋጭነት የሌላቸው ማምረቻዎች ለምሳሌ ያህል የኮንክሪት እና የአስፋልት ባቺንግ ፕላንት የመሳሰሉትን ለመትከል የሚያስፈልግ ቦታ ነው።

3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑና የማይታደስ ሃብት ስለሆነ ሃብቱን ለመጠበቅና በከተማው የስራ እድል በማስፋፋት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ለማሳደግ፣
2. የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ተገልጋዮችን ሊያረካ በሚችል መልኩ ቀልጣፋ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው ለማድረግ፣
3. የከተማውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ክምችት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ ጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃ ለማደራጀትና ተገልጋዮች መረጃውን ብቃት ባለው መንገድ እንዲጠቀሙና የአመራረት ሥራውን ዘመናዊ ለማድረግ፣
4. አካባቢን ያገናዘበና ከስነምህዳር ጋር የሚጣጣም ዘላቂነት ያለው የማዕድን ልማትን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

5. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ለማምረት ፈቃድ በተሰጣቸው ወይም በሚሰጣቸው ግለሰቦች፣ ማህበራት፣ የግልና የመንግስት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የማዕድን ፈቃድ

6. <u>ስለማዕድን ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ሰው የኮንስትራክሽን ማዕድን ምርት ለማምረት ከባለስልጣኑ ፍቃድ ማግኘት አለበት፣
2. ማንኛውም ሰው ለመንግስት ልማትና ለህዝብ አገልግሎት ለንግድ ላልሆነ አላማ ፍቃድ ሰጭውን መስሪያ ቤት በማስፈቀድ የኮንስትራክሽን ማእድን ማምረትና መጠቀም ይችላል፣

3. ህጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ በይዞታ ውስጥ ያለከፍያና ፍቃድ ሳያስፈልገው አምርቶ መጠቀም ይችላል፣ሆኖም ያመረተውን ምርት ሪፖርት ማድርግ ይኖርበታል፡፡

7. ፈቃድ የማይሰጥባቸው ቦታዎች

ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ወይም ስለቦታው የሚመለከተው ህጋዊ አካል ወይም ባለቤት ካልፈቀደ በቀር፡-

1. ለመቃብርና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ቦታዎች፣
2. የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይም ብሔራዊ መታሰብያዎች በቆሙባቸው ስፍራዎች፣
3. ለመሰረተ ልማት አውታሮች በተከለለበት ቦታዎች፣
4. ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ወይም በብሔራዊ ፓርክ በተከለለ ስፍራዎች፣
5. ከመኖሪያ መንደሮች፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ከመሰረተ-ልማት አውታሮች 100 ሜትር ከኤሌክትሪክ ተሸካሚ 25 ሜትር ከወንዝ ዳርቻ 30 ሜትር ክልል ውስጥ ፈቃድ አይሰጥም፣
6. ፍንዳታ ለሚያስፈልጋቸው የማዕድን ማምረቻ ፈቃዶች ፈቃድ ሰጪው መስሪያ ቤት ፍቃድ ሲሰጥ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

8. ፍቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

በአዋጁ አንቀፅ 11 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በማዕድን አዋጅ፣ደንብና በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ የሚከተሉትን ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡-

1. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተግባሩን ማካሄድ የሚችል፣
2. የማእድን ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን መረጃ ማሟላት የሚችል፣
3. ስለቦታው ከሚመለከተው አካላት የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም የውል ስምምነት የሚያቀርብ፡፡

9. ፈቃድ የሚሰጥባቸው የኮንስትራክሽን ማዕድን አይነቶች

1. ጥቁር ድንጋይ፣
2. ገረጋንቲ፣
3. ቀይአሸዋ፣

4. ቀይአፈር፣

5. ነጭ የግንብ ድንጋይ ወይም ጥርብ ድንጋይ፣

6. የወንዝ አሸዋ ወይም ጠጠር እና ሌሎች ተመሳሳይ ማዕድናት ናቸው፡፡

10.<u>የሚሰጡ የፈቃድ አይነቶች</u>

1. የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ፈቃድ

ሀ/ አምርቶ የመሸጥ ፈቃድ፣

ለ/ አምርቶ የመጠቀም ፈቃድ፣

ሐ/ የምርት ማንሻ ፈቃድ፣

መ/ ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መሳሪያ/ማሽን/ መትከያ ፈቃድ፣

ሠ/ ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ፈቃዶች፡፡

## ክፍል ሶስት

## ኃላፊነት እና ተግባር

11. <u>የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በአዋጁ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1. ለማዕድን ሥራዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በመቀበልና ፕሮሰስ በማድረግ ውድቅ ማድረግ ወይም ማፅደቅ፣
2. ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት አዲስ ፈቃድ መስጠት፣ነባር ፈቃድ ማደስ እና ስም ማዛወር፣ ስም ለውጥ ፣የቀረጥ ነጻ ይሁንታ መስጠት እና የማምረት ፈቃድ መሰረዝ፣
4. ከስራው ጋር በተያያዘ ለድንጋይ ወፍጮ መትከያና ተያያዥ ተግባሮች ፈቃድ መስጠት
5. በከተማው የሚገኘውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ወቅታዊ ዋጋና አቅርቦት ማጥናት፣
6. በጥናት የተገኙትን የማዕድን መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ማደራጀትና ማሰራጨት፣

7. ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ወይም ሮያሊቲ፣ የመሬት ኪራይ፣ ሌሎች ክፍያዎች መሰብሰብ፣
8. የአዋጭነት ጥናት እና የተጽዕኖ ግምገማ ሰነዶችን መሠረት ያደረገ የማዕድን ማምረት ዘዴዎችን እና የመልሶ ማልማት ስራዎችን ይከታተላል፣ሙያዊ ምክር ይሰጣል እርምጃም ይወስዳል፣
9. የሚሰጡ ፈቃዶች ጥቁር ድንጋይ፣ ገረጋንቲ፣ ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መስሪያ ማሽን መትከያ ፈቃድ፣ ሌሎች የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፈቃድ ይሰጣል፣
10. በከተማዋ ክልል የሚገኙ የኮንስትራክሽን ማዕድን ቦታዎችን ያጠናል፣
11. በከተማዋ የተሰጡ ፈቃዶችን ማስተዳደር፣ ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና መረጃዎችን ያደራጃል፣
12. ለማልሶ ማልማት የሚውሉ ቦታዎችን መለየት እና ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣
13. በክፍለ ከተማ ደረጃ በተሰጡ ውሳኔዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

12. <u>የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የሚሰጡ ፈቃዶች የነጭ ድንጋይ፣ ቀይ አሸዋ፣ የወንዝዳር አሸዋ፣ ቀይ አፈር፣ የመልሶ ማልማት ፈቃድ እና ሳይንሳዊ ተቀባይነት ያለው አፈር ማስደፋት ፍቃድ ይሰጣል፣
2. በክፍለ ከተማ ወይም በማእከል የተሰጡ ፈቃዶችን መከታተል፣መቆጣጠር እና መረጃ ማደራጀት፣
3. በማዕከል ለሚሰጡ አዲስ እና ነባር ፈቃዶች ሙያዊ አስተያየት ይሰጣል፣
4. በክፍለ ከተማ የሚሰጡ ፈቃዶችን መረጃ ለማዕከሉ ያስተላልፋል፣
5. በክፍለ ከተማው በተሰጡ ፈቃዶች ገቢ ይሰበስባል፣
6. አግባብ ያለው ሁኔታ ሲኖር በክፍለ ከተማው የተሰጡ ፈቃዶችን ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

13. <u>የማዕድን ፈቃድ የውል ዘመን</u>

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድን ፈቃድ ዘመን ፡-

1. ለከፍተኛ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ከፍተኛው አምስት አመት ይሆናል፣

2. ለመካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ከሁለት አመት ያልበለጠ ይሆናል፡
3. ለምርት ማንሻ ፈቃድ ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል፡
4. ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መሳሪያ ወይም ማሽን መትከያ ፈቃድ ዘመን ከማዕድን ማምረቻ ፈቃድ የውል ዘመን ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

14. <u>አዲስ የማዕድን ፈቃድ መስጠት</u>

ለከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. የአመልካች ሙሉ ስም፥ፆታ፥ ዕድሜ፥ ዜግነቱን፥ የትውልድ ቦታውንና የደዘማመልከቻ እና የታደሰ መታወቂያ ማቅረብ፡
2. በህጋዊ አማካሪ የተሰጠ የአዋጭነት ጥናት እና የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሠነድ ማቅረብ ይገባዋል፡
3. አመልካቹ የይዞታ ባላቤትነት መረጃ ከሚመለከተው የክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር እንዲሁም ይሁንታውን ለተጠየቀው አገልግሎት ማዋል ስለመቻሉ የአካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት የይሁንታ አስተያየት በደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡
4. አልሚው የማልማት ፍቃድ የጠየቀው በመንግስት ወይም በራሱ ይዞታ ላይ ካልሆነ ከህጋዊ ባለይዞታ ጋር በጊዜ ገደብ የተወሰነ እና በመመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠ ውል ማቅረብ ይገባዋል፡
5. በተፅዕኖ ግምገማው ጥናት መሰረት በአካባቢው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማስተካከል አስፈላጊ ነው የተባለውን የፋይናንስ ፍላጎት በመስሪያ ቤቱ ስም በተከፈተው የባንክ አካውንት ዋስትና ገቢ ማድረግ አለበት፡
6. ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ልዩ ልዩ የፈቃድ ክፍያ ማጠናቀቅ አለበት፡
7. ባለሥልጣኑ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸው ሌሎች ህጋዊ መረጃዎች ሊያቀርብ ይገባል፡
8. የዋና መስሪያ ቤቱን አድራሻና የወኪሉን ስምና አድራሻ መረጃ ይሰጣል፡
9. ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመሥረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ ያቀርባል፡

15. <u>በእርሶ አደርና በማህበር ለተደራጁ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. ስምና አድራሻ፣

2. ፈቃዱ የተጠየቀበት ማዕድን የሚገኝበት ሥፍራ፣
3. በቦታው የመጠቀም መብት ወይም ባለ ይዞታ ስለ መሆኑ ማረጋገጫ ከአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ማቅረብ፣
4. አርሶ አደሮች እራሳቸው ወይም ልጆቻቸው በማህበር የተደራጁ ከሆነ አግባብነት ካለው ህጋዊ አካል ስለመደራጀታቸው የሚረጋገጥ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ፣
5. አርሶ አደሮቹ በኃ/የተ/የግ/ማ ወይም በሽርክና ወይም በሕብረት ሥራ ማሕበር ተደራጅተው መስራት ከፈለጉ ከላይ በተገለጹት የንግድ አደረጃጀት ቅርጾች ስለመደራጀታቸው ህጋዊና ተገቢ ማስረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፣
6. በአርሶ አደሮችና ከሌላ ድርጅት ግለሰብ ባለሀብት የሽርክና ውሎች በጋራ ለመስራት ቢስማሙ በሌሎች የንግድ እና የፍትሐብሄር ህጎች የተደነገጉት የህግ ይዘቶች እንደተጠበቁ ሆነው የድርሻ ክፍፍሉ በሚመለከተው መልኩ መሆን ይገባዋል፣
   6.1. ይዞታው በህግ የተረጋገጠ የአርሶ አደር ወይም አርሶ አደሮች ከሆነ የአርሶ አደሩ/አደሮች/ የትርፍ ተካፋይነት ድርሻ ከተጣራ ትርፍ ላይ ከ40% /አርባ በመቶ/ ያነሰ መሆን የለበትም፣የሽርክና ተካፋዮች ከአንድ በላይ ከሆነ ከአርባ ከመቶ ድርሻቸውን በይዞታቸው ልክ የሚካፈሉ ሲሆን ስምምነታቸውን ከአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አቅርበው ማረጋገጫ ሊያመጡ ይሆናል፡
   6.2. ይዞታው የመንግስት ከሆነ የይዞታ ባለቤት ለነበሩ አርሶ አደሮች እና ማረጋገጫ ያላቸው አካላት የተጋሪነት ደረጃ ከተጣራ ትርፍ ላይ ከ15% /አስራ አምስት በመቶ/ ያላነሰ ይሆናል፣ ይህም በአዲስ ብድር እና ቁጠባ ተቋም በተከፈተው ዝግ አካውንት አምራቹ ገቢ ማድረግ ይገባዋል፣በየወሩም 7.5 % (ሰባት ነጥብ አምስት ከመቶ ብቻ) አውጥተው የሚጠቀሙ ሲሆን ቀሪው በቀጣይነት በአደራጃቸው አካል አማካይነት ለመነሻ ካፒታልነት የሚያገለግል ይሆናል፣
7. የማዕድን ፈቃድ የሚጠየቁ አርሶ አደር አመልካቾች የቦታው ህጋዊ አርሶ አደሮች ስለመሆናቸው ከከተማ አርሶ አደር ኮሚሽን ማረጋገጫ ማምጣት ይኖርባቸዋል ፡

8. በአርሶ አደር አደረጃጀትም ይሁን በሌላ የሽርክና አደረጃጀት ቅርጽ የተደራጁ አካላት ፍቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መንግስታዊ ግዴታዎችን እና ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይገባቸዋል፡

16. <u>ቀደም ሲል ህጋዊ መረጃዎች ሳያሟሉ ስለተሠጡ ፈቃዶች</u>

1. ይህ መመሪ ከመውጣቱ በፊት አስቀድመው የተወሰዱ ፍቃዶች ከላይ የተጠቀሱት ቅድም ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ የሚታደሱ ሲሆን ፣ለእድሳት የማይመጡ ባለፍቃዶች በቀን ገደብ በተወሰነ ህጋዊ እና ይፋዊ ጥሪ በተቋሙ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይደረጋል፡በዚህ ጊዜ ቀርበው በ15 ቀናት ያላሟሉ አካላት ፍቃዳቸው ይሰረዛል፡

2. አርሶ አደሩን በመንደር ውል ያለ አግባብ በጊዜ ባልተገደበ ውል የያዙ ባለሃብቶች ሆነው ማዕድኑን ጨርሰው ቦታውን ለሌላ አላማ እያዘጋጁ ያሉትን ውሉ ተሰርዞ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ለአርሶ አደሩ ይመለሳል፡፡

17. ማመልከቻዎች ስለሚስተናገዱበት ቅደም ተከተል

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ለአንድ አይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ አንድ አይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ከአንድ በላይ ማመልከቻዎች ከቀረቡለት ማመልከቻዎቹ በቀረቡለት ቅደም ተከተል መሰረት ያስተናግዳል፡

2. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች አንድ አይነት ማእድን በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ጊዜ አንድ አይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ማመልከቻዎቻቸውን አቅርበው ከሆነ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ቅድሚያውን ለመወሰን ማማልከቻዎችን የሚገመግም የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማል፡የቴክኒክ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ስራ እቅድ፡ለሥራው ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠን እና የአመልቺን ብቃት ገምግሞ በውጤቱ መሰረት ቀዳሚውን ይወስናል፡

3. ለሁለት አመልካች ከላይ የተካሄደው የግምገማ ውጤት እኩል ከሆነ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

18. <u>ስለፈቃዶችና የመሬት ኪራይ መዝገብ</u>

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ባዘጋጀው መዝገብ ላይ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ያመለከቱትን በሙሉ ፈቃድ ተሰጥቶአቸው ወይም ተከልክለው ከሆነ ይህንኑ ዝርዝር ይመዘግባል፡

2. ተመዝግቦ በፈቃድ ሂደት ላይ ያለ ማንኛውም የፈቃድ ማመልከቻ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ አመልካቹ ጉዳዩን ሳይከታተል ቢቀር ወይም እንዲያሟላ የተጠየቀውን ማስረጃ

ሳያሟላ ከሶስት ወር በላይ ከዘገየ የፈቃድ ጥያቄውን በራሱ ፈቃድ እንደተወ ተቆጥሮ የፈቃድ ሂደቱ ይቋረጣል፡፡

**19.<u>የምርት ማንሻ ፈቃድ የሚሠጥባቸው ሁኔታዎች</u>**

1. ፈቃዱ ከሚያበቃበት ጊዜ በፊት በአስገዳጅ ሁኔታ ሲቋረጥ፣
2. ፈቃዱ ሲሰረዝ እና ያልተነሳ ምርት ካለ፣
3. በተለያዩ ማንባታዎች ምክንያት የተከማቸ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ሲኖር፣
4. የምርት ማንሻ ፈቃድ የሚሰጠው በባለሙያ በተገመተው ምርት መሰረት እንደምርቱ ብዛት እስከ ሶስት ወር በቅድሚያ ሮያሊቲ በመክፈል ይሆናል፡፡

**20.<u>ነባር ፈቃድ ስለማደስ</u>**

1. በአዋጁ አንቀፅ 27፣29 እና 33 ስለፈቃድ እድሳትና ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣የሚከተሉትን በማሟላት የፍቃድ እድሳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡-
   ሀ/ ከክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት የድጋፍ ደብዳቤ በማቅረብ፣
   ለ/ ባለፈው የፈቃድ ዘመን የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን፣ ግምታዊ ቀሪ የማዕድን ክምችት፣ በአካባቢው ላይ ያስከተለው ተፅዕኖና መልሶ ለማልማት የተወሰዱ ርምጃዎችን እና የቀጣይ ሥራውን እቅድ ዝርዝር መረጃ የያዘ ሪፖርት በማቅረብ፣
   ሐ/ በማዕድን አዋጁ፣ደንብ መመሪያና በፈቃድ ውሉ መሰረት መከናወኑ ሲረጋገጥ፣
   መ/ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ሲቀርቡ፣
   ሠ/ ለከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ፈቃድ የፈቃድ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ180 /አንድ መቶ ሰማንያ/ ቀናት በፊት የእድሳት ጥያቄ ሲቀርብ፣
2. ፈቃዱ ሳይታደስ ከዘገየና ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን እንዲታደስ ከፈቀደ ሳይታደስ ተይዞ የቆየበት አመታት የመሬት ኪራይና የፈቃድ እድሳት እንዲሁም ለዘገየበት በመመሪያው መሰረት ቅጣት ከፍሎ ሊታደስለት ይችላል ፣
3. ቀደም ሲል የቀረበው የአዋጭነት ጥናት ከአምስት አመት በላይ ከሆነና በህጋዊ አማካሪ ከተጠና በነበረው ጥናት ለቀረው ዘመን ከአምስት አመት ላልበለጠ ጊዜ እድሳቱ ሊፈቀድ ይችላል፣

4. የፀደቀ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ከቀረበ በዕድሳት ወቅት የማኔጅመንት ኘላን ማቅረብ ይኖርበታል፣
5. የማዕድን ምርት ወጥቶበት የተጠናቀቀ ቦታ ካለ ከቀረው ይዞታ ላይ በመቀነስ በቀጣይ ሊመረትበት የሚችል የማዕድን ክምችት ላለበት ቦታ ብቻ ፍቃዱ ይታደሳል፣
6. የተቀነሰው ቦታ ሊመረትበት የማይችል በማለት ከመረጃ አንጻር ብቻ በማን እንደተመረተ በካርታ ላይ ሊመላከት ይችላል፣መልሶ እስኪለማ ድርስ የመሬት ኪራይ ከእድሳቱ ጋር እንዲከፈል ይደረጋል ፣
7. የተቀነሰውን ቦታ ባለፈቃዱ ካላለማ ለተደራጁ ማህበራት ለመልሶ ማልማት ፈቃድ ይሰጣል ፣

**21.በአርሶ አደር የግል ይዞታና በማህበር ለተደራጁ የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ እድሳት ስለሚሰጥበት ሁኔታ**

1. ከክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የደህንነት ደብዳቤ ማቅረብ፣
2. ምርቱ በተጠናቀቀበት ቦታ ላይ የመልሶ ማልማት ስራ ስለመከናወኑ የሚገልፅ ሪፖርት ሲቀርብ፣
3. በማዕድን አዋጁ፣ደንብ መመሪያና በፈቃድ ውሉ መሰረት መከናወኑ ሲረጋገጥ፣
4. ባለስልጣን መ/ቤቱ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ሲቀርቡ፣
5. ቦታው የመንግስት ይዞታ ከሆነ ለግል አመልካች አልሚዎች፣ለመንግስት ልማት ድርጅቶች በውላቸው መሰረት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ፡፡

**22.<u>ነባር ፈቃድን ማስፋፋት ወይም ማሻሻል</u>**

በአዋጁ አንቀፅ 33/ቀ/ ፈቃዱ ሌሎች ማእድናትን እንዲያካትት ወይም የፈቃድ ክልሉ የማእድን ክምችቱን የማያካትት ከሆነ የማእድን ክምችቱን ሙሉ እንዲሸፍን ተደርጎ እንዲሻሻልለት የመጠየቅ መብት እንዳለው በተደነገገው መሰረት፡-

1. የማስፋፋት ጥያቄ በማመልከቻ ሲቀርብ፣
2. የማስፋፊያ ቦታው ከነባር ፈቃዱ ኩታገጠም ከሆነ፣

3. የማስፋፋት ጥያቄው አልሚው ከተረከበው ቦታ ከ70 በመቶ በላይ መስራቱ ሲረጋገጥ፣
4. የፈቃዱ ክልል የማዕድናቱን ክምችት በሙሉ የማይዝ ሆኖ ሲገኝ፣
5. አመልካቹ ቀደም ሲል በወሰደው ፈቃድ የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ ከሆነ፣
6. ለአዲስ የማዕድን ማምረት ፈቃድ የተቀመጡት መረጃዎች ሲሟሉ፣
7. ፈቃዱ የሚፀናበት ዘመን ቀደም ሲል ከተሰጠ የማዕድን ፈቃድ ዘመን የማይበልጥ ሲሆን፣

## 23. የማምረቻ ማሽን መትከያ ፈቃድ

ከፈቃዱ ክልል ውጭ ለስራው የሚያስፈልገውን ስፍራ በኪራይ ሲሰጠው የሚችለው፡-

1. የድንጋይ መፍጫ ማሽን መትከያና የምርት ማከማቻ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ላለውና በማምረቻ ካባው ውስጥ በቂ ቦታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፣
2. ምርቱን በግብዓትነት ለሚጠቀሙና የማዕድን ፈቃድ ላላቸው የባቺንግ /የኮንክሪት/ ፕላንት እና ከሚመለከተው አካል የብሎኬት ማምረት ፈቃድ ላላቸው አካላት ብቻ ይሆናል፣
3. ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማዕድን ማምረት ፈቃድ የውል ዘመን መብለጥ የለበትም፣
4. ስለቦታው ለአዲስ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ማግኘት የሚታለፉ ሂደቶችና የሚጠየቁ መረጃዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፣
5. የማእድን ማምረቻው ፈቃድ በታደሰበት የጊዜ ልክ የማምረቻ ማሽን ፍቃዱ ሊታደስ ይችላል፣
6. የመንግስት ፕሮጀክት ለሚያለሙ አካላት ፕሮጀክቱን ከሚያሰራው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይገባቸዋል፣
7. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከተቋማቸው የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይገባቸዋል፣

## 24. ከቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1. በአዋጁ አንቀፅ 73 ፣በማዕድን ስራዎች ማሻሻያ አዋጅ 816/2006 አንቀፅ 27 እና በማዕድን ሥራዎች ደንብ አንቀፅ 32 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከነጭ ድንጋይ፣ከቀይ አሸዋ ወይም ከገረጋንቲ ፈቃድ በስተቀር የኮንስትራክሽን ማዕድን ለማምረት የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሳሪያዎች በአዋጭነት ጥናት ዶክመንት ላይ የተካተቱና አስፈላጊነታቸው ሲረጋገጥ፣

2. በተጨማሪ የመስክ ተሽከርካሪ ለማስገባት ቀደም ሲል የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው ዝርዝር የቀረጥ መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፣

3. ፈቃድ ወስዶ ስራ ያልጀመረና የጠየቃቸው መሳሪያዎች ስራውን ለማስጀመር አስፈላጊ ሆነው ከተገኙ ስራ ያልጀመረበት ምክንያት በመስሪያ ቤቱ ሲታመንበት ብቻ ይሆናል፣

4. የቀረጥ ነፃ መብት ለማግኘት በፀደቀው ጥናት መሠረት ፈቃዱን ከወሰደ ጀምሮ በአምስት አመት ውስጥ ብቻ ለስራ መጀመሪያነት የሚያገለግሉ እቃዎች እና ስራውን በላቀ ሁኔታ አስፋፍቶ ለመስራት የማስፋፊያ ጥናት አስገብቶ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሱትን የማምረቻ እቃዎችን የማስፋፊያ ፍቃዱን ከወሰደበት ቀን ጀምሮ በቀሪው የፈቃድ እድሳት ዘመን ውስጥ የማግኘት መብት ይኖረዋል፣

5. የማዕድን ስራ ፈቃድ ስምምነት ሰነዱ የአዋጭነት ጥናት በቅድሚያ በማዕድን ህጎች መሠረት አስፈላጊው ሁሉ ተሟልቶ መዘጋጀትና አግባብ ባለው የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ባለሙያዎች ተገምግሞ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይኖርበታል፣

6. በባለፈቃዶች የሚቀርብ ከቀረጥና ከታክስ ነፃ ጥያቄ በስምምነት ሰነዱ ሃአዋጭነት ጥናት ላይ ያልተካተተ ከሆነ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም፣ ነገር ግን በደንቡ አንቀፅ 32 ንኡስ አንቀፅ 8 መሰረት በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም ያልተካተተ ማንኛውም ቋሚ ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት የሚቀርብ ጥያቄ የሥራ ፕሮግራም ማስተካከያ ማመልከቻ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ ይስተናገዳል፣

7. ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለታለመለት አላማ ብቻ መዋላቸውን ክትትል ይደረግበታል፣

8. በአዋጁ አንቀፅ 73 ንዑስ አንቀፅ 7 መሰረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳይፈቅድና ተገቢው የጉምሩክ

ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት አይሸጥም፣በተጨማሪም ማከራየትም ሆነ ለሶስተኛ ወገን በምንም መልኩ ማስተላለፍ አይቻልም፡

9. ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ማዕድን ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ወይም ባለፈቃዱ የፍቃድ መብቱን ሲተው ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን አግባብ ባለው የጉምሩክ ሕግ መሰረት ተገቢውን የጉሙሩክ ፎርማሊቲ ፈፅሞ ሊሸጥ ወይም ለሌላ ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ሊያሥተላልፍ ይችላል፡

## 25. ፈቃድ ስለማስተላለፍ

1. ፈቃድ የሚያስተላልፈውና ፈቃድ የሚተላለፍለት ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥያቄያቸውን በማመልከቻ ለፈቃድ ሠጪው መስሪያ ቤት ማቅረብ አለባቸው፡
2. የግብር/ ታክስ ግዴታውን እየተወጣ ያለና የካፒታል ጌይን ታክስም ከግብር አወሳሰን በወጣለት መሰረት የሚጠበቅበትን ዕዳ የከፈለ መሆኑን ማረጋገጫ ከገቢዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡
3. ፈቃድ እንዲተላለፍለት የጠየቀው ድርጅት ህጋዊ ሰነዶች ወይም የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የመመስረቻ ጽሁፍ፣የመተዳደሪያ ደንብና የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርትፊኬት ያቀርባል፡
4. ፈቃድ ለማስተላለፍ የጠየቀው ድርጅት ከሆነ ውክልና ሕጋዊ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ለመስሪያ ቤቱ ማቅረብ አለበት፡
5. ስም ለማስተላለፍ የጠየቀው ባለፈቃድ የማዕድን ማምረት ሥራውን በገባው ውል መሰረት ሥራ ጀምሮ እየሰራ መሆኑን፣ ከልዩ ልዩ ውዝፍ ክፍያዎች ነፃ መሆኑን የአፈፃጸም ሪፖርት አቅርቦ በፈቃድ ሰጭው መረጋገጥ አለበት፡
6. ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቋሚ እቃዎችን በሙሉ አብረው እንዲተላለፉ ወይም ለሌላ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ ማዞር ወይም ቀረጥ ስለመከፈሉ በቀጣይ ክትትል የሚደረግበት ይሆናል፡
7. የፈቃድ ስም የሚዞርለት ድርጅት ወይንም ግለሰብ የአዋጭነት ጥናትና የተፅዕኖ ማምገማ ሰነድ በድጋሚ ማስጠናት አያስፈልገውም፣አስቀድሞ በቀረበው ጥናትና የኢንቫይሮንመንታል ማኔጅመንት ፕላን መሰረት እንዲቀጥል ይደረጋል፡ሆኖም በቀጣይ ለሚጠይቃቸው አገልግሎቶች የራሱን የአዋጭነት ጥናት ማቅረብ ይኖርበታል፡ እንዲሁም የማኔጅመንት ፕላን እንዲያቀርብ ይደረጋል፡

8. ፈቃዱ የሆረው ድርጅቱን በመሸጥ ወይም የድርጅቱን አክሲዮን ለግለሰብ በመሸጥ የአክሲዮኑ አባል በማድረግ ከሆነ የሽያጭ ትርፍ ግብር ወይም የአክሲዮን ትርፍ ግብር የከፈሉበትን ማረጋገጫ ከሚመለከተው ህጋዊ አካል ማቅረብ አለባቸው፣
9. ቀደም ሲል ለመልሶ ማልማት የተያዘውን ገንዘብ ስም የሆረለት ግለሰብ ወይም ድርጅት ገቢ ማድረጉ ሲረጋገጥ ቀድሞ የተያዘው እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

## 26.የፈቃድ ስም ማስተላለፍ ስለማይቻልባቸው ሁኔታዎች

1. ድርጅቱ በኪሳራ ላይ ያለ እና እዳ ጥሮበት ያልከፈለ ከሆነ፣
2. እየፈረሰ ላለ ድርጅት፣
3. በማጭበርበር ወይም የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ለማጭበርበር የሞከረ፣
4. ህጋዊ ሰውነት ላላገኘ ማህበር ወይም ድርጅት፡፡

## 27.የፈቃድ ስም ማስተላለፍ የሚቻልባቸው ምክንያቶች

1. በውርስ፣
2. በሽያጭ ወይም በመዳረግ፣
3. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊተላለፉ ይችላል፡፡

## 28.የፈቃድ ስም ለውጥ

ቀደም ሲል የማዕድን ማምረት ፈቃድ የተሰጠበትን ስም ለመለወጥ ለሚቀርብ ማመልከቻ

1. አመልካቹ ማህበር ከሆነ በቅድሚያ ከንግድና እንዱስትሪ ቢሮ እና ከዝቢዎች ባለሥልጣን እንዲሁም ሌሎች ከሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት ስም የለወጠበትን ተዝቢውን መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፣
2. አመልካቹ ግለሰብ ከሆነ በቀድሞ ፈቃድ ላይ ችግር የማይፈጥር ከሆነ በጥያቄው መሰረት የስም ማስተካከያ ይደረጋል፣

## 29.ልዩ ልዩ ክፍያዎችና አገልግሎቶችን ስለማግኘት

ለተለያዩ መ/ቤቶች የድጋፍ ደብዳቤ ለመፃፍ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

1. አምራቹው ለሽጡት የማዕድን ምርት የሮያሊቲ ክፍያ ክፍሎ ማጠናቀቅ፣
2. በማምረት ስራ ላይ ስለመሆናቸውና ያላቸውን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ማቅረብ፣
3. የማዕድን አዋጅ፣ መመሪያና የፈቃድ ውል ግዴታዎችን ማክበር፣

30. ሮያሊቲ ክፍያ

1. የሮያሊቲ ክፍያ የሚሰላው የፌደራል ወይንም የከተማው አስተዳደር ባወጣው ተመን መሠረት ነው፣
2. የኮንስትራክሽን ማዕድን ለማምረት ፍቃድ ያወጣ ድርጅት ወይንም ግለሰብ በማዕድን ስራዎች አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት ሮያሊቲ ይከፍላል፣
3. የሮያሊቲ ክፍያ የሚታሰበው መስሪያ ቤቱ ባጸተመው የማዕድን ሽያጭ ደረሰኝ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከነባት ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳብ ተሰልቶ ሊከፈል ይችላል፣
4. ለሽያጭ ላልሆነ የሚመረት ምርት ቢሆንም የማዕድን ደረሰኝ በመውሰድ በመስሪያ ቤቱ ባለሙያዎች በሚደረገው ክትትል መሰረት የሮያሊቲ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፣

31. የአገልግሎት ክፍያዎች

1. እያንዳንዱ አልሚ መስሪያ ቤቱ ለሚሰጠው የአገልግሎት ክፍያዎች ይከፍላል፣
2. በአርሶ አደር የተያዘና በማህበር ለተደራጁ የኮንስትራክሽን የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃዶች የካርታ ክፍያ የማይከፈል ይሆናል፣
3. በአርሶ አደር የተያዘና በማህበር ለተደራጁ በክፍያ መመሪያው መሰረት ለመሬት ኪራይ የተተመነውን የመነሻ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

32. መንግስታዊ ፕሮጀክት ያላቸውና የመንግስት ልማት ድርጅቶች

1. የማምረት ፈቃድ ከባለስልጣኑ ማግኘት ይኖርባቸዋል፣
2. በየወሩ ያመረቱትን ምርት ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ወር በገባ የመጀመሪያው ሳምንት ለኖ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
3. የመንግስት ልማት የሚሰሩ የግል ድርጅቶችን በተመለከተ የድጋፍ ደብዳቤ ከሚያሰራው ተቋም ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፣እንደማንኛውም አልሚ ካመረቱት ላይ በወቅቱ ዋጋ መሰረት ለመንግስት ሮያሊቲ ይከፍላሉ፣
4. የመሰረተ ልማት ስራው ከተጠናቀቀ ቦታውን ከሰጠው አካል ስምምነት በማምጣት ለአዲስ የማዕድን ፈቃድ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ፈቃዱን መቀጠል ይችላል፣

33. ለመንግስታዊ ድርጅት የሚሰጥ ፈቃድ ስራውን እያከናወነ ማህበራዊ ልማቶችንና ጎን ለጎን የመልሶ ማልማት ግዴታ ማከናወን አለበት ፡

## 34. የማዕድን ሃብትን ስለመቆጣጠርና መልሶ ስለማልማት

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ባቀረበው የተጽእኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ መሰረት የመልሶ ማልማት ስራዎችን ከማምረቱ ጎን ለጎን በእቅድ በየወቅቱ ማከናወን አለበት፡ይህን ባለመድረጉ ለሚከሰት የህይወትና የንብረት አደጋ ተጠያቂ ይሆናል፡
2. በየሶስት ወሩ ባለፈቃዱ የመልሶ ማልማት አፈጻጸሙን በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡
3. በተጽእኖ ግምገማ ጥናቱ ላይ በተቀመጠው የመልሶ ማልማት እቅድ እና አልሚው ባቀረበው የሶስት ወር ሪፖርት መሰረት ባለፈቃዱ ስራውን በአግባቡ ስለማከናወኑ በሚመለከታቸው የቁጥጥር ባለሙያዎች ቁጥጥር ይደረጋል፡ ሪፖርትም ይቀርባል፡
4. ባለፈቃዱ የማምረት ስራውን በሚያናውንበት ወቅት ለተፈጠረው ገደልና ኩሬ መልሶ እስከሚለማ ድረስ የማጠርና በጥንቃቄ የማስጠበቅ እንዲሁም ውሃ እንዳይቋጥር የማድረግ ግዴታ አለበት፡

## 35. የዋስትና ገንዘብ አጠቃቀም

1. የመንግስት ተቋማት የመልሶ ማልማት የዋስትና ገንዘብ የማያስይዙ ሲሆን የመልሶ ማልማት ስራውን በራሳቸው አከናውነው አስረክበው የሚወጡ ይሆናል፡
2. ለመልሶ ማልማት የሚያዝ ገንዘብ በተመለከተ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በቀጥታ በሚያዝበትና ለዚህ አገልግሎት ብቻ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ስም በተከፈተ የባንክ አካውንት ገቢ ይደረጋል፡
3. አልሚው የመልሶ አልሚ ማህበራትን ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተቋራጮችን አስገብቶ የመልሶ ማልማት ስራው እንዲከናወን ያደርጋል፡ በአግባቡ መከናነወኑን ባለስልጣኑ ባረጋገጠ ጊዜ አምራቹ በሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ መሰረት አረጋግጦ እንዲከፈል ይደረጋል፡
4. ለአርሶ አደርና ለማህበራት የተፈቀደ ከሆነ በውዴታ ግዴታ ውል ገብተው ኃላፊነቱን በመውሰድ የመልሶ ማልማት ስራውን በራሳቸው የሚያከናውኑ ይሆናል፡፡

## 36. ፈቃድ የሚሰረዝባቸው ምክንያቶች

በማዕድን ደንቡ አንቀፅ 20 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ

1. በአልሚው ጠያቂነት ፈቃድ እንዲሰረዝለት በማመልከቻ ሲጠይቅ፣
2. ቦታው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት ለሌላ ልማት ሲፈለግ፣
3. ቀሪው ቦታ በቀጣይ የማያሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ፣በባለስልጣኑ የተናጠል ፍላጎት በደብዳቤ አሳውቆ ሊሰርዘው ይችላል፣
4. የመሬት ኪራይ ውል ዘመኑ ሲጠናቀቅና የውል ማራዘሚያ ስምምነት ማቅረብ ካልተቻለ፣
5. አልሚው ከውል ውጭ በሆነ መንገድ ተደጋጋሚ ሕገወጥ ድርጊት ከፈፀመ፣
6. በማዕድን አዋጅና ደንብ መመሪያ ላይ የተጠቀሱ ግዴታዎችን ካላከበረ፣
7. ማዕድኑ ካለቀ ፈቃዱ ተሰርዞ ለባለይዞታው አግባብ ባለው አካል እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

## 37.የተሰረዙ ፈቃዶች ለሌሎች አልሚዎች የሚሰጡበት አግባብ

1. ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት በቦታው ላይ የማልማት ፍላጎቱን በተዘጋጀው ማመልከቻ ላይ ሞልቶ ማቅረብ ይችላል፣
2. በመንግስት ይዞታዎች ላይ ለመንግስት ተቋማት ማመልከቻ ቅድሚያ ይሰጣል፣
3. የቦታው አመላካች ካርታ ተዘጋጅቶ የክፍለ ከተማው አካባቢ ጥበቃ መረጃውን አጣርቶ እንዲልክ በደብዳቤ አስተያየት ይጠየቃል፣ የደብዳቤው ምላሽ የክፍላ ከተማው አካባቢ ጥበቃ በ5 ተካታታይ የስራ ቀናት ለባለስልጣኑ መላክ አለበት፣ ይህ ካልሆነ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በራሱ አጣርቶ ፍቃዱን ሊሰጥ ይችላል፣
4. ለአዲስ ፈቃድ የሚያስፈልጉ ክፍያዎችንና መረጃዎች አመልካቹ እንዲከፍል ይደረጋል፣
5. ከመሬት ባለይዞታነት ጋር ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ህጋዊ ጥያቄዎች ፈቃድ ጠያቂው ከሚመለከተው አካል መረጃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፣
6. ፈቃድ ጠያቂው ለቦታው አስተድሞ የተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ፣ የአዋጭነት ጥናት እና መሰል ሰነዶች ተዘጋጅተውለት ከነበረ፣ እንደገና ማሰራት ሳያስፈልገው በእነዚሁ ሰነዶች መሰረት ለማከናወን ፍቃደኝነቱን በድብዳቤ በመግለጽ ወደ ስራ ሊገባ ይችላል፣
7. ፈቃድ ጠያቂው ከመሬቱ የኪራይ ውል እና የይዞታ ማረጋገጫ ሰነዶች ጋር የተያያዙ ሰነዶች እስኪያቀርብ ለዝግጅት ጊዜ ፍቃዱ በስሙ ተመዝግቦ እንዲቆይ

እና ጊዜያዊ የአንድ አመት ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል ፣ መረጃውን አሟልቶ እንዳቀረበ የአምስት አመት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

**38.ስለጥፋቶችና የሚወሰዱ እርምጃዎች**

የኮንስትራክሽን ማዕድን ለማምረት ፈቃድ ያወጣ አልሚ በወንጀል ሕግ መሠረት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችሉ ቅጣቶች እንደ ተጠበቁ ሆነው በአዋጁ እና ደንቡ ላይ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**39.ስለማህበረሰብ ልማት ተሳትፎ**

በማዕድን ስራዎች ደንቡ አንቀፅ 41/1/ መሰረት የከፍተኛ ደረጃ ማእድን ማምረት ባለፈቃድ በማህበረሰብ ልማት እቅድ የመሳተፍና ለዚህ የሚያስፈልግ ወጭን መመደብ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ፡-

1. በዚህ መመሪያ መሰረት በመንግስት ይዞታ ላይ የሚሰሩ የማዕድን ኣልሚዎች ማዕድኑ የሚገኝበት ቦታ ባለቤት ለነበሩ አርሶአደሮች ፣በሚመለከተው አካላት ለተደራጁ ሥራአጥ ዜጎች ለሁለት ዓመታት በየወሩ አልሚው ከሚያስገባው ገቢ ላይ የሚሰላ 15 በመቶ ወደ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም በማህበሩ ስም የሚገባ ሆኖ፣ ከሁለት ዓመታት በኋላ ማህበሩ ራሱን ችሎ ይወጣል፣ሌላ ተጠቃሚ ማህበር በተመሳሳይ እንደገባ ይደረጋል፣
2. ለአካባቢው ነዋሪ ማሕበራዊና የመሰረተ ልማት አገልግሎት በየዓመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ የሚሰላ 2% ለማህበራዊ አገልግሎቶች ማዋል አለበት፡፡ ይህ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በየአመቱ ማቅረብ ይኖርበታል፣
3. የፈንድ አጠቃቀም ሪፖርት ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን መቅረብና ባለፈቃዱም በግልባጭ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፣
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተጠቀሰውን ለመፈጸም ያልተቻለ ከሆነና ባለስልጣኑ በበቂ ምክንያት መሆኑን ከተቀበለ ለማህበረሰብ ልማት የሚሰበሰበውን ፈንድ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በቀጥታ በሚያዝበትና ለዚህ አገልግሎት ብቻ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ሥም በተከፈተ የባንክ አካውንት ገቢ አድርጎ ማስረጃ ማቅረብ ይገባዋል፣ ይህንኑ ገቢ ባለስልጣኑ ለአመነበት ማህበራዊ አገልግሎት ሊያውለው ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**40.ስለተጠያቂነት**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**41.መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህንን መመሪያ ባለስልጣኑ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**42.መመሪያው የሚጸናበትጊዜ**

ይህ መመሪያ ከወጣበት ከቀን---------/---------------------2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሲሳይ ጌታቸው

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ስራ አስኪያጅ